**የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት**
**ልሣነ- ሕግ ጋዜጣ**
LISAN HIG GAZETA
OF THE BENISHANGUL — GUMUZ REGIONAL STATE
**የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል መንግስት**
**ም/ቤት ጠባቂነት የወጣ**

18ኛ ዓመትአዋጅ ቁጥር 107
ጉባ/ማንኩሽ/ ሐምሌ 2004

## አዋጅ ቁጥር 107/2004 ዓ/ም

## የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት የዳኞች አስተዳደር ጉባኤን ለማሻሻል የወጣውን አዋጅ ቁጥር 38/1995 አንቀጽ 11 ለማሻሻል የወጣ አዋጅ

<u>**መግቢያ**</u>

የክልሉ የዳኞች አስተዳደር ጉባኤ አዋጅ ቁጥር 38/1995 በተሻሻለው የክልሉ ህገ መንግስት ከመዉጣቱ በፊት የወጣና ከህገ መንግስቱ ጋር መታረቅ በማስፈለጉ፡-

በአዋጅ ቁጥር 38/1995 አንቀጽ 11 የተደነገገው "ልዩ መብት" በህገ መንግስቱ በተደነገገው አላማና መሰረታዊ ግብ አንፃር ሲታይ ለህዝብ ተወካይ አባል ለሆነ ለምክር ቤት አባል የሚሰጥ መሆኑና ይህም ምክር ቤት አባሉ በህዝብ የተጣለበትን ሀላፊነት በአግባቡ እንዲወጣ ለማስቻል ታስቦ የተሰጠ መብት እንጅ ዳኞችን የሚመለከት ባለመሆኑ፣

በተሻሻለው የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት ህገ-መንግስት አንቀጽ 49(3.1) መሰረት የሚከተለው ታውጇል፡-

### አንቀጽ 1 አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል የደኞች አስተዳደር ጉባኤን ለማሻሻል የወጣ አዋጅ ቁጥር 38/1995 አንቀጽ 11ን ለማሻሻል የወጣ አዋጅ ቁጥር 107 /2004 "ተብሎ ሊጠቀስ ይቻላል፡፡

### አንቀጽ 2 ማሻሻል

የዳኞች አስተዳደር ጉባኤን ለማሻሻል የወጣውን አዋጅ ቁጥር 38/1995 አንቀጽ 11 ላይ የተደነገገው "ልዩ መብት" አስፈላጊነቱ በተሻሻለው በክልሉ ህገ መንግስት አንቀጽ 48 ንዑስ አንቀጽ 5 መሰረት ለህዝብ ወኪል እንጂ ለዳኞች ባለመሆኑ ለዳኞች የተሰጠው "ልዩ መብት" በዚህ አዋጅ ተሽሯል፡፡

### አንቀጽ 3 አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በክልሉ ልሳነ ህግ ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

ጉባ /ማንኩሽ/ ሐምሌ26/ 2004 ዓ.ም

አህመድ ናስር አህመድ

የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት ኘሬዚዳንት